# ★ዴሞክራሲያ★

ዴሞክራሲያ ቅጽ 34 ቁጥር 10 ነሐሴ 2001 ዓ.ም.


## ዴሞክራሲ አልባ ችግር አይፈታ

ኢትዮጵያ ሀገራችን በአሁኑ ወቅት እያናወጧት ያሉት የተለያዩ ችግሮች መፍትሔ ሊገኝላቸው የሚችለው በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ብቻ መሆኑ ከግልጽም ግልጽ ከሆነ ቆይቷል ። ነገር ግን ይኸ እንደ በጋ ፀሐይ ግልጽ የሆነ ነገር የወያኔ አባወራዎች በተለያዩ ተንኮሎች ለመጋረድ ሲሞክሩ ቆይተዋል ። አሁንም እነኝህ ዘረኛ አምባገነኖች በዴሞክራሲ ስም ሀገሪቱን በአረጀ ባፈጀ የአንድ ፓርቲ አምባገነን ሥርዓት በመግዛት ላይ ይገኛሉ። የለየላቸው ፀረ-ሕዝቦች ፥ አስከፊ አምባገነን አገዛዛቸውን በዴሞክራሲ ነባቢት አሸሞንሙነውና ሸፋፍነው ቅብዓ ሜሮን ቀብተው ያቀርባሉ ። ከዚህም ብልሀት አንዱ የራሳቸውን አገዛዝ ፕሮግራም እነርሱ ራሳቸው አዘጋጅተው በሚቆጣጠሩት የቀልድ የምርጫ ሂደት ውስጥ በማስገባት ድምፅን እንደ ሸቀጥ ፥ መራጩን ደግሞ እንደ ገበያተኛ ቆጥረው በሕዝብና በሀገር ላይ መቀለድ ነው ። ለጊዜውም ቢሆን ይህ ቀልዳቸው በመሳካቱ ፥ ዜጎችን እንደ የዋህ እነርሱን ደግሞ እንደ ብልህና ጮሌ ይቆጥራሉ ።

በመሠረቱ የሀገሪቱን ዜጎች ፥ ማፍቀርና ማክበር ፥ መፍራትና ማመን ከሁሉ በላይ የፖለቲካ ድርጅቶችና በፓለቲካው መስክ ተዋንያን ከሆኑት ሁሉ ከሚጣልባቸውና በአደራነት ከሚሰጣቸው የፖለቲካ ሥልጣን እንዲሁም ሕዝባዊ ሃላፊነት አኳያ ሲታይ መጠበቅ ያለበት ባህርይ ነው ። ያለበለዚያ ለሕዝብ ቆሚያለሁ የሚሉት አነጋገር ተራ ፕሮፓጋንዳ ከመሆን አያልፍም። ለዚህም ነው ይህ ቅን አመለካከት ባልፉት 17 ዓመታት ባሳዩትና ባደረጉት ድርጊቶቻቸው ሊጠበቅ የማይቻለው። በፖለቲካ ህይወት፥ ከሁሉ በላይ መሠረታዊ ችግር የሚከሰተውና የሚመነጨው፥ የተወሰኑ ቡድኖች የምልዓ-ተ ሕዝቡን ንቃተ ኅሊና፥ ዕውቀትና ተመክሮ ዝቅ አድርገው ሲገምቱ ነው ። ይህ በሽታ ደግሞ በሀገራችን የፖለቲካ ሂደት ተደጋግሞ ተደጋግሞ የተከሰተ የማይድን ተውሳክ ሆኗል ። አንተ ለራስህ ስለማታውቅ፥ እኛ እናውቅልሀለን ሲባል የነበረው የአምባገነኖች ምፀት፥ ዛሬም መልኩንና ባሕርዩን ይዘቱንና ዘዴውን በመለዋወጥ በሀገሪቱ የፖለቲካ ሂደት ውስጥ ከፍተኛ አንቀሳቃሽ ሞተር ሆኖ እያገለገለ ይገኛል ። የአንድ ሀገር የፖለቲካ ሕይወት ሊሰምር የሚችለው ፥ ከመጀመሪያው አንስቶ ሕዝቡ ሲቻል በቀጥታ ያ ካልሆነ ደግሞ በሚመርጠው ወኪሉ አማኝነት ሙሉ ተሳትፎ የሚያደርግበትን ሥርዓት ሲያረጋግጥ ነው ። ይህ ከሆነ ደግሞ ለሕዝቡ ከራሱ የበለጠ ማንም

እንደማያውቅለት በተጨባጭ ሊያረጋግጥ ይችላል ። ከዴሞክራሲ መሠረታዊና ዓይነተኛ ዕሴቶች መካከል አንዱ ፥ የዜጎች ቀጥታና ሙሉ ተሳትፎ የመጀመሪያውን ረድፍ መያዙ አሌ የሚባል አይደለም ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ እንኳን ዛሬ ወትሮም ቢሆን፥ የሚሠራለትንና የሚሠራበትን፥ ጠንቅቆ አውቆ የሚረዳ ሕዝብ ነው። መሪዎቹ፥ ሲያምናቸው እየከዱት፥ ሲያከብራቸው እየናቁት፥ ሲያፈቅራቸው እየጠሉት ኖረዋል። ሲያጠፉ እንዲያርሙ ጊዜ እየሰጣቸው ቢቆይም እንኳ ፥ ያው በመጨረሻ ዕድሜያቸው ሀገሩን አጥፍተው ሲጠፉ በተደጋጋሚ አይቷል ። ታዝቧል ። ባለጌን ሲያከብሩት የፈሩት ስለሚመስለው ፥ የኢትዮጵያ አምባገነኖች ሁሉ የሕዝቡን ክብር እንደ ፍርሃት ይቆጥሩታል ። ይህ ክስተትና ሂደት ፥ ከእንግዲህ ወዲህ መልሶ እንዲመጣ ኢትዮጵያ ሕዝብ አይፈልግም።

በሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ላይ አተኩረን የዴሞክራሲን ምንነትና አስፈላጊነትም ስንገነዘብ፥ የቃሉን ትክክለኛ ትርጉም ለመፈለግ የግሪኮችን የፖለቲካ ፈላስፎች የነአርስቶትልን ገለጻ ማገላበጥ የሚያሻን አይመስለንም ። በመሆኑም ፥ የዲሞክራሲን ሥርዓት ለሀገራችን ስንመኝ ይህ ሥርዓት በኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ ፥ ባሕል፥ ዕምነት፥ ሥነልቦና፥ ፍላጎትና ራዕይ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ስናረጋገጥ ነው ። ይህን መሠረታዊ ክስተት ያላገናዘበ ማነኛውም የፖለቲካ ሥርዓትም ሆነ የመንግሥት ምሥረታ ለሀገራችንና ለዜጎቿ ይጠቅማል ብለን አናምንም ። የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፍልስፍና መመስረት የሚኖርበት በሀገር በቀል ዕሴቶችና በዜጎቿ መስተጋብር ላይ ነው ብለን እንመኛለን ። በመሆኑም የተደጋገመ መሪር አገዛዝን ተሸክመው ሊኖሩ የሚችሉ ፥ የዋሆች ናቸው ሊባል ቢቻልም፥ በፖለቲካው ውሳኔ አወሳሰድና ሂደት ፥ የሕዝቡ ተሳትፎ መሠረታዊ ነው። ታዲያ ተፈራራቂ አምባነኖች የሕዝቡን መከራ ቻይነትና ወሰን አልባ ትዕግስት ማለቂያ የሌለው እየመሰላቸውና ለትዕግስቱም የየዋኅነት ትርጉም እየሰጡ ከታላቅነቱ የመነጨውን ይህን ትዕግስቱን ሲፈታተኑበት ኖረዋል ። የዲሞክራሲን ሥርዓት የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት ፥ እንደ አመቻቸው እንደሚገለባብጡት ሁሉ ፥ ሥልጣን በአጋጣሚ በመያዛቸው ብቻ አዋቂ የሆኑ እየመሰላቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ ታላቅነትና ትዕግስት ለራሳቸው መሰሪ ተንኮል በመጠቀም ብልጣ ብልጥ የሆኑና ሕዝብ ያታለሉ ቢመስላቸውም፥ እራሳቸውን እየደለሉና እያሞኙ መሆናቸውን ለመገንዘብ ይቸግራቸዋል ። ሕዝቡን ለማታለል ሳይሆን ፥ ራሳቸውን ለማሞኘትና ለመደለል ሲጠቀሙበት ይታያል። ምክንያቱም፥ የማንኛውም አምባገነን ሥርዓት አራማጆችና አቀንቃኞች ሕዝብን በሃሰት ፕሮፓጋንዳ ለማታለል በሚጥሩበት ጊዜ ሁሉ፥ የኋላ የኋላ የሚታለሉትና የሚወናበዱበት እነርሱ ራሳቸው እንጅ ሕዝቡ ስለማይሆን ነው ። አንድን ሕዝብ ለጥቂት ጊዜ በተከሰተ ግብታዊ ሁኔታ ማሳሳት ይቻል ይሆናል ፥ ሁልጊዜ በማታለል ግን ዘለዓለም መግዛት የሚቻል አይሆንም ። የትግዕስትንና የማታለልን የዕድሜ ርዝማኔ አስተውሎ ለተገነዘበ ሰው፥ አታላይ ገዥዎች ተጣድፈው ሲጠፉ፥ የትዕግስት ባለቤት የሆነው ምልዓተ-ሕዝብ ግን በዘለዓለማዊነቱ የሚቀጥል መሆኑን ይረዳል። ለዚህም ነው ለጊዜው ገዝቼ ካልሆነም አጥፍቼ እጠፋለሁ ካልሆነ በስተቀር በሃያ አንደኛው

*ምዕተ-ዓመት የሚኖረውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ቢቻል በፕሮፓጋንዳ እያታለልኩ÷ ያ ካልሆነ ደግሞ÷ በጠመንጃ አፈሙዝ እገዛለሁ ብሎ መነሳት÷ከጤናማ አዕምሮ የሚመነጭ ሃሳብ ሊሆን አይችልም ::*

*ኢትዮጵያ እንደ ኅብረ-ብሔርነቷና እንዲሁም የተለያዩ ፈላጭ-ቆራጭ ሥርዓቶች የተፈራረቁባትን ያህል÷ ዜጎቿ ካገኙት ተመክሮ ሊቀሰም የሚገባ መሠረታዊ ትምህርት ቢኖር ÷ ከእንግዲህ ወዲህ የአምባገነን አገዛዝ ቦታ ሊኖረው የማይገባ መሆኑን ነው :: የቆየውን የረዥም ዘመናት የፖለቲካ ሕይወትና የመንግሥት ሥርዓት እንኳ ለጊዜው ለታሪክ መዝጋቢዎች ትተን÷ ካለፉት አምሳና ስድሳ ዓመታት ወዲህ ያለውን ዕውነታ ብናጤን÷ የዴሞክራሲ ቃና ቀርቶ ÷ ጠረኑም ያልነበረና የሌለ መሆኑን ለመረዳት አንቸገርም :: በተለያዩ አመለካከቶችና ርዕዮቶች አማካኝነት ግን የዴሞክራሲን አስመሳይ ጥብቆ ባጠለቁ ቡድኖች አራማጅነት በሕዝቡ ላይ ተዘርዝረው የማያልቁ ግፍና በደሎች መፈፀማቸውን አይተናል:: አሁንም እያየን ነው:: አምባገነኖች በተፈራረቁ ቁጥር የሚያመረቅዘውን ይህን ፀረ-ዴሞክራሲ ሂደት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በምድረ-ኢትዮጵያ ዳግመኛ እንዳይከሰት ለማድረግ የሚቻለው ÷ ወያኔና የመሠረተው ሥርዓቱ የችግሮቹ ዋና ምንጭ መሆናቸውን በመገንዘብና በቆራጥ ትግሉም አስወግዶ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚሳተፍበትና የሚወስንበት ገደብ የለሽ የዴሞክራሲ ሥርዓት ሂደት ሲጀመር ነው:: ያኔ ሰላምና መረጋጋት እየሰፈነ፤ ብሔራዊ አንድነቱን እየጠበቀ፤ ሉዓላዊነቱንም እያስከበረ፤ጣልቃ እየገቡ ሂደቱንም ሊያሰናክለት የሚፈልጉትን ባዕዳኖች እንዳመጣጣቸው እየመከተ፤ በመካከሉ የሚገኙ ጥቃቅን ልዩነቶችና የፖሊሲ አቋሞችን በዴሞክራሲ ውይይትና አርቆ አስተዋይነት በተሞላበት መልክ እየፈታ ሲሄድ÷ ለችግሮቹ በሚያቀርባቸው መፍትሄዎችና በሚወስናቸው ውሳኔዎች መልካም ውጤት ማስመዝገቡ የማይቀር ይሆናል:: ይህም ስኬታማ ይሆን ዘንድ ደግሞ በአንድ ብሔር ስም ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ ሀገርና ሕዝብ የሚያጠፋው ዘረኛ ቡድን ከሥልጣኑ መነሳት/ መወገድ ይኖርበታል :: በአንድ ብሔር ስም ብቻ ተደራጅቶ የራሱን ብቸኛ የፖለቲካ ፕሮግራም በሚያራምድ ዘረኛ ቡድን ፈላጭ ቆራጭነት ሥር ሆና÷ ኅብረ-ብሔራዊት ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅሟ ሊጠበቅ ከቶ አይችልም :: ይህ ሁኔታ እስካለ ድረስ ደግሞ ÷ አሳታፊ ዴሞክራሲ ይከሰታል ተብሎ የሚታሰብ አይሆንም :: ወደፊትም ቢሆን በተመሳሳይ ሁኔታ ሥልጣን ለመያዝ የሚመኙና የግል አጀንዳቸውን ብቻ ለምሳፈፀም የሚያስቡ ሁሉ÷ የሚገጥማቸው ሕዝባዊ ተቃውሞ ብርቱ እንደሚሆን ከግንዛቤ ማስገባቱ ለሁሉም የሚበጅ መሆኑን እንጠቁማለን :: ለዚህም ነው ጠቅላላው የሀገራችንን የፖለቲካ መልከዓ-ምድር የመለወጡ ጉዳይ ÷ ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ሥርዓት ምስረታ እንደ ቅድመ-ዝግጅትና ቅድመ-ሁኔታ ሊቆጠር የግድ ይላል የምንለው::*

*በሀገሪቱ የመከላከያ ተቋም ስም የሠራዊቱን አወቃቀር÷ አሰራርና እንቅስቃሴ በራሱ ብሔር አባላት ብቻ ቁጥጥር ሥር ባደረገ ቡድን መዳፍ የምትገዛዋ ኢትዮጵያ÷ የመረጃውንና የስለላውን መዋቅር ከላይ እስከታች አሁንም በዚሁ ብሔር አባላት እጅ አስገብቶ ሕዝቡን አፍኖ እየገዛ ሥልጣን ላይ ካለ*

ቡድን፥ በሀገራችን የዴሞክራሲ ብሩኅ ተስፋ ይመጣል ብሎ ማንም ኢትዮጵያዊ አያስብም። ወያኔ አዲስ አበባ በገባ ማግሥት ፥ የራሱን የፖለቲካ ፕሮግራም ለጊዚያዊው የሥልጣን መቆናጠጫ እንዲጠቅመው በማሰብ፥ ሰልቆና ለንቁጦ፥ አብኩቶና ጠፍጥፎ፥ እንዲሁም፥ ለባዕዳን ተንበርካኪነት እንዲጥም አድርጎ በማዘጋጀት "ብሔራዊ ጉባዔ" ጠራሁ ብሎ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እንደቀለደ የቅርብ ትዝታና ተመክሮ ሊሆነን ይገባል ። የወያኔ " ብሔራዊ ጉባዔ " ጊዚያዊው ተልዕኮው፥ ሥልጣኑን የሚያደላድልብትን ሁኔታ መፍጠርና ለሀገሪቱንም መከፋፈል መሠረት መጣል ሲሆን ፥ ቋሚ ዓላማው ደግሞ ለኢትዮጵያ በሂደት መፈረካከስ ማጠየቂያ የሚሆኑ የ"ሕግ" ሰነዶቹን አዘጋጅቶ እነርሱን በተግባር ማዋል ነበር። ለጊዜውም ቢሆን ሁለቱም ተሳክተውለታል። ይህን ብሔራዊ በደል በፅናት ይቃወማሉ ያላቸውን ኢሕአፓንና ሌሎች ድርጅቶች በጉባዔው እንዳይሳተፉ አበክሮ የታገለውም ያለምክንያት አልነበረም ። ይህንን እንዲያደርግ የልብ ልብ የሰጡትም ምዕራባውያን ለመሆናቸው በኢትዮጵያ ሕዝብ የኅንለ ደም ልብ ውስጥ ተቀምጧል። የወያኔ የጡት አባቶች ይህን ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ በደል በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ሲፈፀም መተባበር ባልተገባቸውም ነበር ። ይህ ኢትዮጵያን እንደቅርጫ ፍሪዳ የቆራረጠው ጉባዔ ከተሳተፉት መካከል ስብሰባውን በመቃወም የቁርጥ ቀን ዜግነታቸውን ያስመሰከሩ አንድ ኢትዮጵያዊ ሰማዕት እንደነበሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያስታውሰው ነው ። የኢሕአፓ ሰማዕታትም ግንባር ቀደም ሚናቸውን ተጫውተው አልፈዋል ። የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች መሆናቸውን ካስመሰከሩት መካከል፥ የፓርቲው አመራር አባል የነበረው ሰማዕቱ ገብረ እግዚአብሔር (ጋይም) በግንባር ቀድም የሚጠቀስ ጓዳችን ነው ። በአንፃሩ በዘመነ ደርግም ሆነ በወያኔ፥ የኢሕአፓ የብሔራዊ ጉባዔም ሆነ የሽግግር መንግሥት ጽንሰ-ኃሳብ፥ ይዘትና ባሕርይ፥ ዓላማና ግብ፥ ለሀገራችን ዘላቂ ራዕይ የሚጠቅም ሆኖ የሚቀርብና ሁሉንም የሀገሪቱ ዜጎች የሚያሳትፍ ኢትዮጵያዊና ብሔራዊ፥ ቋሚና መሠረታዊ ሰነድ ነበር። ሥልጣን ለመያዝ ለአቋመጠ ብድን ተብሎ የሚዘጋጅ ባለመሆኑ ፥ ከወያኔው ፀረ-ኢትዮጵያ ሰነድ ጋር መቸም ቢሆን የማይጣጣም ይሆናል።

ኢሕአፓ ለኢትዮጵያ የሚመኝላት ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት፤ለአንድ የፖለቲካ ቡድን፥ወይም የብሔር ድርጅት ዓላማ ማስፈፀሚያ አይደለም። ወይም ደግሞ በግርግር ሥልጣን ላይ ለመውጣት በሚመኙ በሂደት ግን በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያላቸውን ጥላቻ ለሚገልፁ ቡድኖች ሲል አይደለም። የፓርቲው የዲሞክራሲያዊ ሂደትና ራዕይ፥አግላይ ሳይሆን፥ ሁሉን አሳታፊ፥ ኀጠኛ ሳይሆን ብሔራዊ፥ ጊዚያዊ ሳይሆን ዘላቂና ቋሚ ነው። በሀገሪቱ የወደፊት ሕገ-መንግሥት ውስጥ ሊካተቱ የሚገባቸውን አንኳር አንኳር ጉዳዮች አንቀጽ በአንቀጽ መዘጋጀት በዲሞክራሲያዊ ሂደት ውስጥ ዓይነተኛ ሚና ይኖራቸዋል ተብሎ ይታመናል። የሀገራችን ችግሮች ሁሉ በአንድ ትውልድ ዘመን ይወገዳሉ የሚል ብዥታ ስለማይኖር፥ ለዘለቄታ ችግሮች ዘለቄታ መፍትሔ ለመፈለግ ለሚረዱት ኃሳቦች ሁሉ መሠረት መጣል ይገባል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊጤን የሚገባው ጉዳይ ቢኖር፥ የኢትዮጵያን ሥር የሰደዱ ችግሮች ፥ እንኳንስ ባእዳን ቀርቶ፥ ስንቶቹ የፖለቲካ ድርጅቶችና ስብስቦች የቱን ያህል የጠለቀ ዕውቀት እዳለቸው ለማወቅ የሚነሱ ጥያቄዎች መኖራቸውን ነው ። የጥያቄዎቹ ሰበብ ፥ እንዲያው በዘልማድ ከሚነሳ የመቸገርና የመጨነቅ መንስዔ ሳይሆን፥ ራሱን የቻለ ምክንያት ያለው ይመስላል። ለአንድ ተውሳክ መድኃኒት ሊገኝለት የማይቻለው፥ ራሱን በሽታውን መርምሮ ለማግኘት ስለማይቻል በመሆኑ ነው ከተባለ፥የኢትዮጵያ ችግር እስካሁን መፍትሔ ሊገኝለት ያልተቻለው፥ ምናልባት ችግሩና መንስዔው ምን እንደሆነ ጠንቅቆ ለመረዳት ስለአልተቻለ ነው ቢባል ፥ ጥያቄውና መልሱ የተዛባ ነው ማለት አይቻልም። ያማ ባይሆን ኖሮ፥የተቃዋሚው ክፍል፥ በሀገሪቱ ችግር መፍትሔ ላይ ለመረባረብ በቻለ ነበር። እስካሁን እንደታየው ከሆነ፥ በሀገሪቱ መፍትሔ ፍለጋ ላይ መስማማት ቀርቶ፥ ላለመስማማት እንኳ መስማማት አልተቻለም።ለዚህም ይመስላል፥ብዙዎቹ ድርጅቶች ራሳቸው ፈልገው ያላገኙትን የሀገሪቱን ችግር መፍትሔዎች ከባዕዳን ቤት እናገኛለን ብለው የሚማስኑት ። የኢትዮጵያን ችግር መፍትሔ ለመፈለግ የሚደረገው ሂደት የአንድን ትውልድ ዘመን አገባድዶ ወደ ሚቀጥለው ትውልድ ለመሸጋገር የበቃውም ፥ መፍትሔው አልገኝም ብሎ በመደበቁ ሳይሆን ችግሩንና መፍትሔውን ለማገጣጠም ስላልተቻለ ይመስላል ። ዞሮ ዞሮ ግን የሀገሪቱን ሥር የሰደዱ ችግሮችን መፍታት የሚችለው እራሱ ባለቤቱ የችግሩ ተቋዳሽ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑ አይካድም ። የኢትዮጵያን ችግሮች ለመፍታት ቀላጤና ባዕዳን ችሎታ ይኖራቸዋል ብለን አናምንም ። ይህ በሀገራችን የውስጥ ጉዳይ የባዕዳን መግባትን የምንቃወመው ከመርኅ አኳያ ብቻ ሳይሆን፥ የራሳችንን ጉዳይ ለማስተናገድ ብቃቱና ኃላፊነቱ የኛው የራሳችን ብቻ መሆን ይገባዋል ብለን ስለምናምንም ጭምር ነው ። ታዲያ የኢትዮጵያ ሕዝብ የራሱን ችግር ራሱ ይፍታ ተብሎ ለእርሱ ከተተወለት፥ በሀገሪቱ ውስጥ ገደብ የለሽ ዴሞክራሲያዊ ሂደት የመጀመሩ ጉዳይ አማራጭ አይኖረውም ። የኢትዮጵያን ሕዝብ ሙሉ ተሳትፎን ያገኘ ዴሞክራሲያዊ ሂደት ደግሞ ለማንኛውም ጉዳይ መፍትሔ ማግኘት የሚሳነው አይሆንም ። ይህ አሳታፊ ዴሞክራሲ ሂደት በበርካታ የአፍሪካ ሀገሮች ከሞላ ጎደል እየተካሄደ ውጤቶችን በተጨባጭ ማስመዝገቡን ስናይ ፥ የሀገራችንን ዕጣ ፋንታ ለመርገም እንገደዳለን። የኢትዮጵያ ሕዝብ የራሱን የፖለቲካ ሕይወት ለመምራት የፖለቲካ ተሳትፎ ዕድል ለምን እንደሚነፈገው ፥ ግራሞታቸውን የሚገልጹ የፖለቲካ ታዛቢዎች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም።

በዕርግጥም፥ "የፊተኞቹ የኋለኞች ይሆናሉ" የተባለው ቃል በትክክል በተግባር የታየው ፥ ዘለዓለም የታሪክ ምፀት ሰለባ ሆኖ በሚኖረው በሀገራችን ሕዝብ ላይ መሆኑን ስንረዳ፥ ሀዘናችን እጥፍ ድርብ ይሆንብናል። ምክንያቱም፥ ማንኛቸውም የአፍሪካ ሀገሮች ገና ከቅኝ ተገዥነት ነፃ ከመውጣታቸው በፊት በነፃነቷ ኮርታ የነበረች ሀገር ኢትዮጵያ ብቻ መሆኗን ስለምንረዳ ነው ። የዓለም ሀገሮች የተለያዩ ቅርፅና ይዘት ባላቸው ሥርዓተ-መንግሥታት ሥር የሚተዳደሩ መሆናቸውን ብንረዳም፥ እናም ደግሞ ሁሉም ሀገሮች በየመንግሥታቱ ሥርዓቶች ረኪዎችና ተደሳቾች ይሆናሉ ብለን

ባንገምትም፥ እንደ ዛሬይቱ ኢትዮጵያ በዘር ላይ የተመሠረተ ሥርዓትና ዜጎቿም ተገነጣጥለው እንዲበታተኑ የሚያዝ የህገ-መንግሥት አንቀጽ አላቸው ብለን አናስብም። ይህ ግንዛቤ እንዳለ ሆኖ ግን ፥ ሁል ጊዜ ስለ ሀገራችን ጠቅላላና ዝርዝር ሁኔታዎች እየተነተኑ ብቻ ቢቀጥሉ የኢትዮጵያን ሁኔታ ይለውጠዋል ማለት አንችልም ። ሊለውጠው የሚችል ፥ ፀረ-ዴሞክራሲ የሆነው የዘረኞቹ አምባገነን ሥርዓት ተወግዶ በዴሞክራሲ ሥርዓት ሲተካ ብቻ ነው ። ይህ ሥርዓት ግን በየአራቱ ዓመታት የይስሙላ ምርጫ አካሂዳለሁ ብሎ ያሾፋል ። በጭላዳዎች የተሞላው የወያኔ ፓርላማ ፥ ከዝኆጀሮ ቆንጆ መካከል ለወያኔ አገልጋይ የሚሆኑትን አዳዲስ ግብረ-በላዎች ለመምረጥ ካልሆነ በስተቀር፥የኢትዮጵያን የፖለቲካ፥የኢኮኖሚና የማኅበረሰባዊ ችግሮችን ይቀርፋል ተብሎ የሚጠበቅ አይሆንም። "ሲፈጭ የነበረ ሲነፋ ከበረ" የሚለውን ይትበሃል ወያኔዎቹ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማሾፊያ ይጠቀሙበት ካልተባለ በስተቀር ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወያኔ አገዛዝ ተላቅቆ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሊመራና ሊተዳደር የሚገባው ታላቅ ሕዝብ ነው።

ኢሕአፓ ባሳለፈው መራራ የትግል ሂደት ካካበታቸው ተመክሮዎች አንዱ ከማንኛቸውም ድርጅቶች በተሻለ ሁኔታ የወያኔዎቹን ማንነትና ምንነት በሚገባ ማወቁ ነው ። ይህም በመሆኑ ባሕርያቸውንና አሠራራቸውን በተለያዩ ገፅታዎች በብቃት እየተከታተለ ሲታገላቸው ኖሯል ። ይህም ሂደት በጠነከረ መልኩ ይቀጥላል። ምንም እንኳ ወያኔ፥ ሕዝቡን ለማወናበድ በማር የተለወሰ ፕሮፓጋንዳና መፈክር ቢያነበንብ፥ ኢሕአፓ ቀድሞ ሕዝቡን ከማስጠንቀቅና የአደጋ መከላከያ ምልክት ከማሳየት/ከማሰማት ወደኋላ ብሎ አያውቅም። ለዚህም ነው ወያኔና ኢሕአፓ የማይታረቅ ቅራኔ አላቸው ተብሎ መናገር የሚቻለው ። ወያኔ በኢሕአፓ ላይ ያለውን ጭንቀትና ፍርሀት በመጠኑም ቢሆን እፎይታ ሊሰጠኝ ይሆን ብሎ በመመኘት ሰርስሮ ለመግባት ሞክሮ ሳይሳካለት ቀርቷል ። ለሙከራው ስኬታማነት ይበጁኛል ብሎ ያላቸው ከሃዲያን ሊጠቀም ሞክሮም ጥረቱ ከሽፎበታል።

የዴሞክራሲ ሥርዓት ከአምባገነኖች በምፅዋት የሚቸር ሳይሆን ፥ በሕዝብ ትግል የሚገኝ መሆኑን የዓለም ሕዝብ ታሪክ ሕያው ምስክር ነው። ለአምባገነኖች የሚደረግ የባዕዳን ትብብርና የቅጥረኞች እንደ እስስት መለዋወጥ ለሀገራችን ዕውነተኛ ዴሞክራሲም ይሁን ዘላቂ ሠላም አያስገኝም ። ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና ተያይዞም መረጋጋትና ሠላም ከሌለ ደግሞ ልማትና ዕድገት የሚባሉ ነገሮች አይኖሩም ። የኢኮኖሚ ዕድገት ኖሮ ዜጎች ኑሯቸው ካልተሻሻል ደግሞ ፥ ረሃብ ቸነፈሩ፥ ድኅነቱና በሽታው አግጥጦ-አፍጥጦ መቀጠሉ አይቀርም ። የእነኝህ ሁሉ ድምር ውጤት ደግሞ የማይቀረው ሕዝባዊ አመፅ ነው ። ሕዝባዊ አመፅን ያረገዘ ሕብረተሰብ ደግሞ ጠቅላላ ሀገር አቀፍ አብዮታዊ ፍንዳታ አምጥቶ ከጭቆና ለመገላገል እንደሚነሳ የካቲት 1966 ዓ.ም አስመዝግቦ ያለፈው ሕዝባዊ ቅርስ ነው። የሀገራችን ችግር፥በጥግንግንና በውሽልሽል ዋገምት ተበጥቶ የሚድን አደለም ።

የኢትየጵያ ሕዝብ ግን ወያኔን ፥ ምከረው ምከረው ያለበዚያ መከራ ይምክረው ብሎ ከወሰነ ቀይቷል ። እኛም ዛሬም እንደትላንቱ የትግል ሰልፋችን ከምንታገልለት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር መሆኑን ማንም ሊጠራጠር አይችልም ። በአምባገነኖች ውደቅት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንደ ሚገነባ የታሪክ ሀቅ ነው ። ጆሮ ያለው ይስማ !!!